# የታሪክ ክህደት በማንዴላ የስንብት ፆሎት ላይ ሲደገም!!

አንተነህ ሽፈራው - ታህሳስ 9/2006 ዓ.ም/Dec 18, 2013

በኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላት አገሮች ሁለንተናዊ ከፍተኛ ድጋፍ የወያኔ የጎጠኝነት ወታደራዊ ክንድ በመፈርጠሙና በኋላም በመንገድ መሪነት የወሎን፣ የጎንደርንና የጎጃምን ሕዝብ ትጥቅ ያለ ብዙ ወጣ ውረድ በማስፈታት ባገለገሉ በነ ታምራት ላይኔ ተዋናኝነት ወያኔ መላ አገሪቷን በግንቦት 1983 ዓ.ም በዚሁ ወታደራዊ ክንዱ መውረር መቻሉን ተከትሎ በተፈጠረው አዲስ ዓይነት የጎሣ/የቋንቋ/ ፖለቲካ አደረጃጀት እነ ሆድ-ባምላኩ ወዲያው ለዚሁ የወያኔ የጎሣ/የቋንቋ/ ፖለቲካ አደረጃጀት ሴራ ሰለባ በመሆን የጋራ ኢትዮጵያዊ ቤታችንን ለማፍረስ ከመሞከር አልፎ እርቆ በመሄድ ወያኔ በጠላትነት/በኢትዮጵያዊነት የፈረጀውን የሕብረተሰብ ክፍል ለያቶ በመግደልና በማፈናቀል በታሪክ፣ በትውልድና በሕግ ፊት የሚያስጠይቅ ተደጋጋሚ ወንጀል እየፈጸሙ መሆናቸውን ላለፉት 23 ረጅም የመከራ ዓመታት በግልፅ እያየን ነው።

‘ፈረንሣይኛ ቋንቋ የሚናገሩ የፈረንሣይ አገራባች አገሮች ሁሉ ፈረንሣዊ ነህ/ነው (በፈረንሣይ ግዛት ውስጥ ይጠቃለላሉ) የተባለ ይመስል’ ምንም ዓይነት ተቀባይነት በሌለው መስፈርት የኢትዮጵያን ሕዝብ በቋንቋ ሰበብ ከመከፋፈል አልፎ በመሄድ ይባስ ብሎም ሕብረተሰቡ የማይፈልገውንና የማይገባውን እንዳዲስ ቋንቋ እንዲማር ማስገደድና ወደፊትም የሚበጅህን እኔ አውቅልኃለሁ በማለት የአንድን የሕብረተሰብ ክፍል መጻዒ ዕድል ፋንታን በግዳጅ መወሰንና አስፈላጊ ከሆነም ደግሞ ከቀየው ጭራሽ ማፈናቀል ከወንጀልም አልፎ ዘር ማጥፋት መሆኑን ወያኔና የጎሳ ፓለቲካ ሰለቦቹ ጠፍቷቸው አይደለም - - - የቋንቋ መስፈርት ኢትዮጵያዊነትን ማዳከሚ ስልት ሆኖ እስካገለገላቸው ድርስ በቀጣይነት የሚጠቀሙበት መሪ ሓሳብ ስለሆነ እንጅ!!

አማራውን ትግሬ ነህ አልያም በግድ ኦሮሞ ካልሆንክ ብሎ ማስገደ አይደለም ዛሬ ኦሮሞ ነህ ተብሎ በአንድ ክልል ውስጥ እንዲታጎር የተደረው የባራይቱማ፣ ኢቲቲኡ፣ ሁምባና፣ ቦራና፣ አቢትችሁ፣ ሳዱትችሃ፣ አፍራ-ጉድሩ ዝርያና ጎሣዎች እንኳ በአንድ የኦሮምኛ ቋንቋ የሚግባቡ አለመሆናቸው ይታወቅል። ይህ በመሆኑም ያለፈ ታሪካቸው ትቢያ እንዲሆን ተደርጎ አዲስ የላቲን ቋንቋ ተፈጠረላቸው።

እጅግ በጣም የሚገርመው ደግሞ የወያኔ የጠዋት ጠንሳሾቹ/መሪዎች/ በተለያዩ ምክንያቶች በአካል እርቀዋቸው ባሉበትና በሂደት ደግሞ የዚሁ ሴራ የበላይ መሃንዲስ የነበረው መለስ ዜናዊ ከመካከላቸው በሞት በተለየበት ግዜ እንኳን ሳይቀር " . . . ምን ላመሉ ዳቦ ይልስ" እንዲሉ ሆነና የዚሁ የመለስ ዜናዊ የሙት መንፈስ የማይለቃቸው በመሆኑ ያው የተለመደ የተላላኪነት ባሕሪያቸው ሳያሳፍራቸው ፀረ-ኢትዮጵያዊ ሥራቸውን ዛሬም ድረስ በማን አለብኝነት መንፈስ በዓለም አቀፍ መድረክ ሳይቀር ይዘውት የወጡ መሆኑ ነው።

ለዚህ ጽሑፍ መነሻ የሆነኝም ይሄው በማንዴላ የመጨረሻ ስንብት የሕሊና ፆሎት ስነሥርዓት ላይ ኢትዮጵያ ለፀረ-አፓርታይድ ትግሉና ለሌሎችም የአፍሪካ የነፃነት ትግል እንቅስቃሴዎች የመደራጃ ማዕከል በመሆን የተጫወተችውን ከፍተኛ አሥተዋፆ ከፍተኛ ቦታ በመስጠት ኢትዮጵያን በመወከል የወያኔው ጠ/ሚ ንግግር እንዲያደርግ ፕሮግራሙን በሚመራው አካል በከፍተኛ ክብር በተጋበዘ ግዜ ‘ጀሮአችን ምን ሊሰማ’ እንደሚችል በቴሌቭዥን መስኮት በፆሞና ብንጠብቅም ነገሩ ያው 'ካባብ እንቁላል እርግብ መጠበቅ' ሆነና ከኃ/ማሪያም ደሳለኝ ኢትዮጵያ ለኤንሲ/ANC ና ለሌሎች የነፃነት ታጋዮች ያደረገችውን ከፍተኛ አስተዋፆ በተገኘው መልካም አጋጣሚ ለማስረዳት አለመፈለጉ ብቻ ሳይሆን አንድም ግዜ እንኳ የኢትዮጵያን ስም መጥራት አለመቻሉ የቱንም ያህል እንኳ የወያኔ ተላላኪ ቢሆን ያን ያህል እርቆ በመዝቀጥ የተፈጽሮ ስብዕናውን በከንቱ ለሚያልፍ ንዋይ አሳልፎ መሥጠቱ አመልከዋለሁ በሚለው አምላክ ፊትም እንኳ ቢሆን እጅግ በጣም የሚያሳፍር ተግባር የፈፀመ መሆኑን መታዘብ መቻሌን ለማመላከትና በዚህ ጉዳይ ላይ ኢትዮጵያውያን ልብ ብለው የራሳቸውን ግንዛቤ እንዲጨብጡ ለመጠቆም ነው።

የኃ/ማሪያም ደሳለኝ ወደ መድረኩ በክብር መጋበዝም ዋናው ዓላም ኢትዮጵያ ለማንዴላና ለኤንሲ/ANC/ ያበረከተችውን ልዩና ታላቅ ታሪካዊ አስተዋፆ በተገኘው አጋጣሚ ኢትዮጵያ ለዓለም ሕዝብ እጥር ምጥን

አድርጋ በኩራት እንድታሳውቅ ታስቦ እንጅ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ስለማንዴላ ማንነት ትንታኔ እንዲሰጥ አለመሆኑ በሚገባ ይታወቃል - - - ያንማ ሌሎች እውቀቱ ያላቸው መናገር ይችሉ ነበርና። በዚያች የግዜ ጥበት ውስጥ ኃ/ማሪያም ደሳላኝ ኢትዮጵያ ለማንዴላና ለኤንሲ/ANC/ የነበራትን ቅርበት እንዲናገር ታስቦ የተሰጠውን ዕድላ በአግባቡ መጠቀም ባለመቻሉም መድረኩን በሚመሩት አካባቢ አላስፈላጊ ግዜ እንደባከነባቸው ቆጥረው ሊቆጩ እንደሚችሉ መገንዘብ አያዳግትም። እኔን እጅግ በጣም የገረመኝ ደግሞ ኃ/ማሪያም ስለማንዴላ ማንነት ትንታኔ ለመስጠት ምንም ዓይነት የፖለቲካና የሞራል ብቃት እንደለሌው ሰነዱን አስይዘው ለላኩት ወያኔዎች አስቀድሞ መናገር አለመቻሉ ነው።

የኃ/ማሪያምን አስከፊ ንግግን ለዋቢነት ለመታዘብ ያህል ለኤንሲ/ANC ከኢትዮጵያ ያነሰ አስተዋፆዖ ታደርግ የነበረችን ታንዛኒያን በመወከል በርዕስ ብሔሩ ጃካያ ኪክዌቴ /Jakaya Kikwete/ የቀረበውን ንግግር ላንዴም እንኳ ቢሆን ማዳመጡ በቂ ነው - - - ታንዛኒያና ዋና ከተማዋ ዳር-እ'ሰላም /Dar Es Salaam / ከ20 ግዜ በላይ በርዕስ ብሔሩ ንግግር ውስጥ የንግግር አሳሪ ጉዳዮች ሆነው በኩራትና በክብር ተነስተዋል። እናም በወቅቱ ኢትዮጵያን ወክሎ የሚቀርብ አንድም ተቆርቋሪ አካል ሊኖር ባለመቻሉ ይሄው የታንዛኒያው ርዕስ ብሔር ንግግር የኢትዮጵያን መልካምና ታሪካዊ ውለታ ለግዜውም ቢሆን በዚያ ታሪካዊ መድረክ ላይ ጠቅልሎ ወሰደው። ". . . የበሬን ምስጋና ወሰደው ፈረሱ ይባል የለ!!"

እዚህ ላይ አንድ ልብ ልንለው የሚገባ ዐብይ ጉዳይ ቢኖር በተቃዋሚው ጎራ ነን በሚለው አካባቢም ቢሆን የኢትዮጵያን ታሪክ እንደ እሬት የሚመራቸው መኖራቸውን ደግመን ደጋግመን ማየት እየቻልንም ነው። እንዲያውም ያለፈ ታሪክ የሚነሳ ከሆነ ቀጣዩን የአብሮነት ጨዋታ ያበላሽብናል ብለው በመርህ ደረጃ በአደባባይ ሊያስተምሩ እየሞከሩ ነው። ይሁን እንጅ ይህ ዓይነቱ ግንዛቤ መሠረተ ቢስና ከግዜአዊ ጥቅምንና የኃይል ሚዛን አሰላለፍን እያዩ ብልጣብልጥና ወቅታዊ ፖለቲከኞች የሚያራምዱት ስልት ከመሆን አይዘልም- - - አልሸሹም ዞር አሉ ዓይነቶች!!

እናም የኃ/ማሪያምን ዕይን ያወጣ አስከፊ ንግግር ስናዳምጥ ወያኔ በራሱ ሴራ በዙሪያው ያሰባሰባቸው የነ ሆድ-ባምላኩን ማንነት በገሃድ የታዘብንበት መድርክ ብቻ ሳይሆን በተቃዋሚው ጎራም ውስጥ አለን የሚሉ የታሪክ አጣማሚዎችና ጠላቶች አደገኝነት ጭምር ደርበን እንድናይ የረዳ ጥሩ አጋጣሚ ነበር።

እርግጥ ነው ይህ በማንዴላ የስንብት የሕሊና ፆሎት ላይ የቀረበው የኃ/ማሪያም አስከፊ ንግግር የወያኔው የሰኔው 1983 ዓ.ም ኢትዮጵያውያን ድርጅቶችንና ተቆርቋሪ ግለሰቦችን ከሽግግር መድርኩ ኮንፍረስ እንድንገለል የተደረግንበትና በኋላም ይህን አፍራሽ ኮንፍረስ ተከትሎ ኤርትራን ሕጋዊነት በሌለው አግባብ በጦረኝነት ስሜትና ትቢት ብቻ ከኢትዮጵያ እንድትገነጠል የተደረገበት ሴራ ቅጽያ መሆኑ ስለሚታወቅ ብዙም አይገርመንም።

የማንዴላ እልፈተ ሞት በተለያዩ የዜና ተቋማት ለዓለም ሕዝብ በተሰማ ግዜ ለዚህ ጀግና ሰው መታሰቢያ ትሆንልኝ ዘንድ አጭር የስንኝ ቋጠሮ ለማቅረብ ሞክሬ ነበር - - - ላንባቢ ላደረሱልኝ ለኢቶሚዲያና ለሌሎችም ድሕረ ገፆች ምስጋና ይድረስና!! ከዚያች የስንኝ ቋጠሮ ውስጥ አንዷን የሰበዝ ስባሪ መዘን ብናወጣት እንደሚከተለው ትነበባለች፡- ቀጥሎ ያለውን ሊንክ ይጫኑት ባንዳ አገር ሳይመራ!!

*"እንዳሁኑ ሳይሆን አገር ሳይቆረስ ባንዳ አገር ሳይመራ፣*

*ነፃነት ሳይናቅ አንድነት ሳይላላ በነ-ሆድ ባምላኩ በወያኔ ሴራ፣*

*ዳዳው ሳይራቆት ንብረት ተዳጉዞ ወደ አንድ ጎተራ፣*

*ኢትዮጵያ ነበረች የትግል ተምሳሌት ለአፍርካ - ለኤሺያ ለነቻጉቤራ::*

*. . ."*

እናም ነገሩ ባንዳ አገር እመራለሁ በሚልበት ክፉ ዘመንና እነ ሆድ-ባምላኩ ደግሞ በተላላኪነት ተግባራቸው ኢትዮጵያን ወክለው መቆም በማይችሉበት አንደበት ታሪክን አዛቡ ብለን ብናብድ ከንቱ ራስን ከመጉዳት የዘለለ ምንስ ይፈይዳል? ጥሩነቱ እነሱ እየመሰላቸው ነው እንጅ ታሪክ በታሪክነቱ ምንግዜም ይኖራል- - - i.e., neither we overwrite it nor we destroy it. Whether it is bad or good, it always remains and exists as it happened. የአንድ አገር ታሪክ የሕዝቧ የረጅም ግዜ የደም ፍሰትና የአጥንት ክፋይ ውጤት መሆኑ መረሳት የለበትም:: ታሪክ የሌለው ሕዝብ ውስጡ ባዶ ነው - - - ማንነትም የለው (no matter what kind of it was? It shall be kept as it happened!):: ለዚህም ነው ኢትዮጵያ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የረጅም ግዜ ታሪካዊ ቁርኝት ውጤት ናት የምንለው::

ያለፈ ረጅም ታሪካችን የወደፊቱ መነሻ መሠረታችን መሆኑ ለአፍታም ቢሆን መረሳት የለበትም (ጥሩው በጥሩነቱ ጎጅውም በጎጅነቱ ትምህርት የሚወሰድበት ነውና):: ታሪክን ለመሰረዝና ለመደለዝ መሞከር ደግሞ የመጀመሪያው የክህደት ተግባር ነው:: ክህደትን ተከትሎ ማስተጋባት ደግሞ በክህደት ቁልቁለት ካሓዲን ተከትሎ መንጎድ ይሆናል - - - ልክ እንደ ወያኔና እንደነ ሆድ-ባምላኩ ዓይነት:: *We can't overwrite history; it always remains as it happened. Event, time, and space are key attributes of history.*

ምንም እንኳን ከላይ ለማመላከት እንደሞከርኩት ለዚህ ጽሑፍ መነሻ የሆነኝ በማንዴላ የመጨረሻ የስንብት የሐሊና ጸሎት ላይ የኃ/ማሪያም ደሳለኝ ያቀረበው አሳፋሪ የክህደት ንግግር ቢሆንም ቅሉ በተለያዩ መድረኮች ላይ ታሪክን የማዛባት ተግባር ላለፉት 23 የወያኔ አስከፊ አስተዳደር ዓመታት ሲከናወን እያየን ነው:: እዚህ ላይ ላነሳ የፈለጉት ግን የአፄ ምኒልክ 100ኛ ዓመታት እልፈተ ሞትን ተንተርሼ ከትቂት ወራት በፊት በVOAና ና በሌሎች ዜና አቅራቢዎች ዘንድ "ወጣቱ ሙሁርና የፖለቲካ ተንታይ/አናሊስት" እየተባለ የሚሞካሸው ጃዋር መሐመድ "ጃዋርኛ/Jewarism/ አክራሪ እስልምና ስብከቱን በሰበከበት መድረክ ላይ ያቀረበው ትንታኔ እሱ እንደሚለው ሳይሆን በ16ኛውና በ17ኛው ክፍለ ዘመን ግዜ በግልባጩ ከደቡብ እስከ ምሥራቅ ኢትዮጵያና ከዚያም ሸዋን አልፎ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ወሎ ድረስ ለመዝለቅ ሲባል የተፈፀመውን ወረራና ጭካኔ የተሞላበት ጭፍጨፋ መዳሰስ ነው:: ሙሉውን ንግግር ለመስማት ይጫኑት [የጃዋሪዝም]!!

ጃዋር በዚያ ትቢት በተሞላበት ወያኔአዊ አደበቱ አፄ ምኒልክ በታሪክ የሚታወቀውን የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ከሆቶማን ቱርክና ግብፅ ተደጋጋሚ ወረራ ለመከላከልና ለማስከበር በሚል በሥልጣን ዘመናቸው ግዜ ወደ ደቡብና ምሥራቅ ኢትዮጵያ ያደረጉትን አገራዊ ዘመቻ "ወረራ" አድርጎ ለማቅረብ ሞከረ:: ትክክለኛው ታሪክ ግን ጃዋርኞች/Jewarist/ና የወያኔ የጎሣ ፖለቲካ ስለቦች አጣመው እንደሚያቀርቡት ሳይሆን በተገላቢጦሽ ወረራና ጭፍጨፋ የተፈፀመ በአያትና ቅድመ አያት ባድማው ላይ ይኖር በነበር ኢትዮጵያው ሕብረተሰብ ላይ በወቅቱ "የገዳ ሥርዓትን" ይከተሉ በነበሩ የሕብረተሰባችን ክፍሎች ከደቡብ ባሌ ጫፍ ተነስተው ወደ ምሥራቅ፣ ምዕራብና ሰሜን የኢትዮጵያ ግዛቶች ባደረጉት የተስፋፊነት ወረራ እንጅ እሱ ተወረረ በሚለው ሕብረተሰብ ላይ አለመሆኑን ታሪክ ይመሰክራል:: ይህንም እውነተኛ አሳፋሪ ታሪክ ለአብሮነት ቅድሚያና ከፍተኛ ቦታ በመስጠት እኛ ወደ ጎን ስንተወው እነሱ ግን አስቀድመው ታሪክን ማጣመም ይመርጣሉ - - - ያውም ግራ ቀኝ የነበረውን ግድፈት/ያለፈ ጎጂ ተግባር/ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ማየቱን ፍፁም ቸል ብለው::

ከላይ በገዳ ሥርዓት ብዬ ለመጠቆም የሞከርኩትን ጽንሰ ሓሳብ ትንሽ ገፋ አድርገን ለማየት ብንሞክር <በገዳ ሥርዓት> እያንዳንዱ እርከን ስምንት ስምንት ዓመታት የሚቆዩ ስድስት እርከኖች ያሉት ሲሆን በተለይ በሦስተኛውና በአራተኛው እርከን (Luba/Class) ላይ የሚገኙት የሥርዓቱ አባላት ሙሉ ተግባራቸው አዳዲስ አካባቢዎችን ጭካኔ በተሞላበት (በጃዋርኛው) መንገድ ነባሩን ሕብረተሰብ ቢቻል ሙሉ በሙሉ በመግደል (ግድያ መበጣልና) ያ የማይቻል ከሆነ ደግሞ በማፈናቀል (ከተጠቂው አካባቢ መቋቋም የሚኖር ከሆነ ደግሞ ሰፈሩን በሳት በማቃጠል ጭምር) መውረርና በቁጥጥር ስር የዋለውን አዲስ አካባቢና ንብረት ከኋላ ሆነው ለሚከተሏቸው ሽማግሌዎች (በገዳ ሥርዓት በስድስተኛው እርከን ላይ ለሚገኙት )፣ እንዲሁም ሴቶችና እፃናት አስረክበው ሌላ አዲስ ወረራ ለመፈፀም ወደፊት መገስገስ ነው:: የዚህ እርከን መሪዎችም አባ ዱላ፣ አባ ቦኮ ተብለው ይጠራሉ - - - ልክ እንደ ዛሬው የወያኔው አባ ዱላ!!

*"…the Savannah and the semi-desert which they inhabited to the south of Bali could no longer support their growing numbers and their herds and Galla began to move into the southeastern peripheries of the Ethiopian plateau. The struggle between Gran and Christian Ethiopia undoubtedly facilitated the Galla migration into the highlands. But this expansion was later curbed by Gran's armies and by Gelawdewos…" [Abir, pp. 136-7, 1980]*

*"…Supreme efforts were needed in Serse Dingil's last years, therefore, to maintain the road between Gojjam, Damot and the southwest open and to protect Gojjam against Galla attacks." [Abir, p. 163, 1980].*

*"By 1570, exploiting the topography of Amhara and the character of its government and population, the Baraytuma began to raid westwards into Ethiopia's heartlands, as far as Gojjam and Dembiya. In the 1570s and 1580s, using Angot and Amhara (where the Wollo group began to settle) as their main bases they (mainly the Karayu-Azebu) pillaged Tigre, Begemder, northern Showa and parts of Gojjam. The Borana renewed their westward advance immediately after the departure of Serse Dingil in 1572. No longer hampered by the network of Chewa and the presence of royal army, they submerged the southern provinces **and by 1576/7 penetrated Showa**. In the coming years the numerous clans of the Mecha group moved west of Showa and began to raid Damot and nearby territories. Concurrently, their Tulama brothers began to settle in western and norhwestern Showa and to raid Gojjam across the Abbay. During the 1580s, while the Abitchu penetrated southern Showa, the Mecha and related groups occupied Bizamo and overran a large part of Damot. From there or from Showa their Sadetcha clans continued to expand towards the Omo-Gibe basin while, at the same time, their Afra-Gudru clans reached the Abbay from the south and increased their pressure northwards on Gojjam and westward on Damot." [Abir, p.164, 1980].*

ይህ የጃዋርና የወያኔ ጎሣ ፖለቲካ ሰለባ የሆኑ ሴረኞች የፈጠራ ታሪክ የኦሮሞ ሕብረተሰብ እንደ ሌላው ኢትዮጵያዊ ሁሉ አሁን በጋር ለምንኖርባት ኢትዮጵያ አገራችን ያደረገውን እጅግ በጣም መጠነ ሰፊ የታርክ ድርሻ ዋጋ በማሳጣት ኢትዮጵያዊነቱን በማቆሸሽና በአዲስ አገር ፈጠራ ልቦናው እንዲሰለብ በማድረግ ኢትዮጵያን ለማዳከም የታሰበ ሴራ እንጅ እውነታው ከፍ ብሎ ያለው መሆኑን ጠፍቷቸው አይደለም:: ውሸት ሲደጋገም እውነት ይሆናል በሚል ብሂል/ታክቲክ/ አዲስ ታሪክ እየፈጠሩ ኢትዮጵያን ማዳከምና በአገር ላይ አገር መፍጠርን ግብ አድረገው!!

ምንም እንኳን ጃዋር ለሰበከው የፀረ-ኢትዮጵያና ክርስትና ሃይማኖት ስብከት መልስ ለመስጠት መሞከር አሁን ከተነሳሁበት አጀንዳ ጭራሽ የሚያወጣኝ ቢሆንም ጹሑፌን ከመቋጨቴ በፊት ግን ጃዋር በዚያ ወያኔአዊ ትቢተኛ የታሪክ ፈጠራ ንግግሩ በምሥራቅ ኢትዮጵያ/በሐረር/ የነበረውን ቅርስ በመጠበቅ ረገድ ኦሮሞዎች ተጫወቱ ያለውንና በግራኝ መሃመድ ጦርነት ግዜ ፖርቹጋል በጦር ኃይሏ ኢትዮጵያን እንዳገዘች አድርጎ ያቀረበውን እውነትነት የሌለውን የፈጠራ ታሪክ እጅግ በጣም ባጭሩ እንደሚከተለው ልዳስ - - - የሚከተለውን የታሪክ መረጃ ላቅርብ::

ግራኝ መሓመድ ከምሥራቅ ኢትዮጵያ ተነስቶ የኢትዮጵያን ታሪካዊ ቅርሶችና ቤተክርስቲያንን እያቃጠለ ጎንደር ደንቢያ ላይ በተደረገው የጦፈ ጦርነት እ.ኤ.አ 1543 ዓ.ም ወያና-ደጋ (ደንቢያ) ከአፄ ገላው-ዲወስ ጋር አብሮ በዘመተ የፖርቹጋል ዜጋ በተተኮሰች ጥይት ሕይወቱ ካለፈች በኋላ ግራኝና የግራኝ መሃመድ የጦር መሪ የነበረው 'ኑር' ይመሩት የነበረው የጅሃድ ሰራዊት ወዲያው በመበታተኑና የምሥራቅ ኢትዮጵያ (በተለይ ደግሞ ሐረር) ና አካባቢው ከባሌ አካባቢ በፈለሱ ጎሣዎች በመወረሩና ታሪካዊ ቅርስም መውደም የመጀመሩ ዜና ለኑር እንደደረሰው ወዲያው ከጎምደር ደንቢያ ወደ ሐረር በመመለስ የተከፈተውን ወረራ ለመቋቋም ቢሞክር

አስቸጋሪ ስለሆነበት ቢያንስ ቢያንስ እንኳን የተወሰነ ታሪካዊ የእስልምና ቅርስ ከተከፈተው አዲስ ዓይነት ወረራ ለመታደግ በሚል ኑር የአካባቢውን ሕብረተሰብ አስተባብሮ ዛሬም ድረስ በምልክትነት ያለውን ታሪካዊ ግንብ የጦር ምሽግ እንዲሆነው አስቦ እንደገነባ አደረገ::

*"…Thus, exploiting the absences of Nur (ኑር የግራኝ መሃመድ እጅግ በጣም ታዋቂ የጦር መሪ ) and the bulk of the Muslim army, the Galla overran most of Harar's territories and threatened the town proper. It was in this period, during the cycle of luba „Mesle", (1556-1564), that the pattern of the Baraytuma"s expansion changed dramatically and became a full-scale migration." [Abir, p. 137, 1980]*

*"Nur „the Just and Pious" is even more glorified by Harari traditions that Gran „the Conqueror" because he saved Harar from the Galla and dedicated himself to its protection. Nur's armies continued to hold most of Waj and Fatagar even after 1560, when they were reported to have been defeated by Hamalmal. But rather than carrying on the traditional war against Ethiopia, from 1559 to the time of his death in 1567, Nur gave his undivided attention to the growing pressure of the Galla. Although Nur was unable to dislodge the Galla from the parts of the Chercher-Harar plateau which they had overrun and settled, his tireless campaigning and the wall which, according to tradition, he had built around the town, temporarily curbed the advance of the Baraytuma and saved Harar. " [Abir, p. 137, 1980]. Highlighted colour added.*

በቅርቡ ጋዜጠኝ ተመስገን ደሳለኝ 'የምሥራቅ ኢትዮጵያ ፖለቲካ ክፍል ሁለት' በሚለው መጸፃፉ በገጽ አንድ ላይ ግንብን አስመልክቶ የሚከተለውን ትክክለኛ ታሪክ ዘግቦ ነበር "ቋንቋን መሰረት ያደረገው ኢህአዴግ ሰራሹ ‹ፌደራሊዝም› አወቃቀር የሀገሪቱ መፃኢ ዕድል የተቋጠረበት ‹የሰዓት ቦንብ› መሆኑን ለመረዳት የምስራቅ ኢትዮጵያዋን ሐረር እንደ መሳያ መውሰዱን ግድ የሚያደርጉ በርካታ ገፊ ምክንያቶች አሉ፡፡ እንደሚታወቀው የሐረር ከተማ አመሰራረት ብዙሃኑ ህዝብ ከሚኖርበት ‹ጀጎል› ከተሰኘው በግንብ የተከለለ ቅፅር ጋር ይያያዛል፡፡ በ16ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ራሳቸውን ከብሔር ወረራ ለመከላከል በአካባቢው ነዋሪዎች እንደታነፀ በርካታ ድርሳናቶች የሚናገሩለት ጥንታዊውና ታሪካዊው የጀጎል ግንብ . . . ነው፡፡" ማድመቅ በእኔ የተጨመረ!!

*"The Baraytuma Galla, especially the Ittu, Humbana and Karayu tribes, renewed their advance in the Chercher-Harar plateau." [Abir, p. 138, 1980].*

*". . . the Baraytuma swept the area and destroyed many hamlets and villages as fas as the hirterland of Zayla. The town of Harar itself was besieged for a time and had it not been for the timely arrival of reinforcements from the coast it might also have fallen to the Galla. . . ." [Abir, p. 139, 1980].*

*". . . Harar, however, gradually declined because its economy was adversely affected by the occupation of most of its lands by the Galla . . . "the fortunes of Zayla were always closely connected to those of Harar. It was, therefore, badly affected by Harar's decline and the deterioration of law and order in the whole region"" [Abir, p. 140, 1980].*

*"As the Baraytuma began their advance into the Harar-Chercher plateau and along the verges of the eastern escarpments in the 1550s they gradually vacated Bali with its excellent grazing lands and left it to their Borana brethren." [Abir, p. 150, 1980].*

Hamalmal was the powerful military figure of Gelawdewos and later to Minas. When Gelawdewos died in battle with Adal in 1559, Minas (r. 1559-1563) the third son of Queen Mother Sebla Wengel of Gojjam was crowned in Gojjam to succeed

Gelawdewos. And the cousin of the young king Hamalmal was given more power in the southeast and its peripheries. His confrontation with Nur gave the Galla an ample chance to spread around Harar and its peripheries.

እርግጥ ነው ግራኝ መሃመድ በጥይት ተመቶ ደንቢያ ላይ የወደቀ አንድ ቤተመንግሥት አካባቢና አብሮ ከንጉሡ ጋር በዘመተ የፖርቹጋል ዜጋ መሆኑን መካድ አይቻልም። ሆንም ግን ፖርቹጋል የኢትዮጵያ መሪዎች የሚከተሉትን የኦርቶዶክስ ክርሥትና ሃይማኖት ወደ ካቶሊክነት እንዲለውጡ ጫና ታደርግ ስለነበር ከፖርቹጋል ወደ ኢትዮጵያ የመጡት የንጉሱ አማካሪዎችና እጅ አዋቂዎች የግራኝ ጦርነት ከመጀመሩ በፊት ጀምሮ ወደ መጡበት እንዲመለሱ እየተደረገ ያለበት ከመሆኑ ባሻገር ፖርቹጋል በወቅቱ ስፔንን በቅኝ ግዛት ይዛ ታስተዳድር የነበር በመሆኑ እንግሊዝ ደግሞ የፖርቹጋልን የስፔን ቅኝ ገዥነት አጥብቃ ትቃወም ስለነበር (ስፔንን ለራሷ ትፈልግ ስለነበር) በግራኝ ጦነት ወቅት ሁለት ኃያላን አገሮች እጅግ በጣም በከፉ ጦርነት ውስጥ ነበሩ።

በተለይ ደግሞ ፖርቹጋል በኢትዮጵያው ውስጥ ለተቀሰቀሰው የግራኝ ጦርነት ለንጉሱ ታግዝ ይሆናል ብላ እንግሊዝ በመፍራት ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባውን የባሕር መስመር (እንግሊዝ) ዘግታ በመያዝ የፖርቹጋልን የባህር ላይ መርከቦች ዝውውር በጦር ኃይሏ ታጠቃ ነበር። በዚህም የተነሳ ሆቶማን ቱርክና በአባይ ወንዝ ጉዳይ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላት የሆነችው ግብጽ ለግራኝ መሃመድ የሚያስፈልገውን ዘመናዊ የጦር መሣሪያና የጦር አማካሪ በስፋት ሲያቀርቡ ኢትዮጵያ የፖርቹጋልን እገዛ ብትፈልግም እንኳ እንግሊዝ የፖርቹጋልን የባህር ላይ መተላለፊያ መስመሩን ዘግታ በመያዟ እገዛው ሊገኝ አልቻለም።

ይህ ከላይ ለማየት የሞከርነው ትክክለኛው ታሪክ ሆኖ እያለ የኢትዮጵያ እስላሞች በክርስቲያን ፖርቹጋል ጭምር እንደተወጉ አድርጎ ጃዋርኛ የፈጠራ አክራሪ ታሪኩን አሜሪካ ላይ ሆኖ መስበክ ጀመረ - - - አገር ቤት ቢሆን ኖሮ ስንቱን ክርስቲያን ኢትዮጵያዊ በጨፈጨፈው ነበር ብዬ ከምር ከማዘኔ ባሻገር ለመሆኑ ጃዋር የኦሮሞ እስላሞች ተቆርቋሪ መሪ ሆኖ መቅረብ የሞከረ እሱ ራሱ መቸና የት እስልምና ሃይማኖቱን መከተል እንደጀመረ ገባ ብሎ ቢያስረዳን? እኔ እንደሚገባኝና በታሪክም እንደምንረዳው የጃዋር ለእስልምና ሃይማኖት መሪነቱ ከጳጳሱ ቄሱ ዓይነት  እዳይሆን እንጅ የኢትዮጵያ እስላምና ክርስቲያን ወገኖች እጅግ በጣም ተከባብረውና አንዱ ያንደኛውን ንብረትና ሃይማኖት ጠብቀው የኖሩ መሆናቸውን ነው። ሌላው ቀርቶ ቤተክርስቲያን በድንገተኛ የእሳት አደጋ እንኳን ሲቃጠል የኢትዮጵያ እስላሞች ከክርስቲያን ወገኖቻቸው ጋር በመሆን ውኋ ይዘው እሳት የሚጠፉ መሆናቸውን ለአፍታም ቢሆን መረሳት የለበትም - - - እንደዛሬው የወያኔ ካድሬ እስልምና ሃይማኖት ተከታዮች የሚባሩቁበት ዘመን ሳይመጣ።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!